የሰበር መ/ቁ. 16896

ጥቅምት 16 ቀን 1998

ዳኞች፡ - 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

**አመልካች፡** - ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

**መልስ ሰጪ፡** - የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ

*ውል - የውል ጉዳይ አወሳሰን - የውሎች ውጤት፡ -*

*የፍትሐብሔር ሕግ 1711፣ 1731/1/*

አመልካችና መ/ሰጪ በገቡት ውል አንቀጽ 24 ግራ ቀኙ እርስ በእርሳቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል በሚለው ድንጋጌ ክርክሩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም በማለት አመልካች ጉዳዩ በሽምግልና እንዲታይ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጐ የኢሉባቦር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ውሣኔ በመስጠቱና ውሣኔው በበላይ ፍ/ቤቶች በመጽናቱ የቀረበ አቤቱታ፡፡



**ውሣኔ** የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት አላቸው፡፡
2. በህግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው፡፡
3. የተጠቀሰው የውሉ ድንጋጌ አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚታይ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ፍ/ቤት ይህንኑ ተፈፃሚ ማድረግ አለበት፡፡

ጥቅምት 16 ቀን 1998

የመ/ቁ. 16896

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. ወ/ሮ ደስታ ገብሩ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ጠበቃ ወርቅዬ አባይነህ ቀረበ፡፡

መልስ ሰጭ፡- የኢሊባቡር ዞን ትምህርት መምሪያ - ቀረበ

<u>ፍርድ</u>

ለሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በኢሊባቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ መልስ ሰጭ የአሁኑ አመልካችንና ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ በተባለ ድርጅት ላይ ውልን መሠረት አድርጉ በአጠቃላይ 184.559.26/አንድ መቶ ሰማንያ አራት ሺ አምስት መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከሃያ ስድስት ሣንቲም/ እንዲከፈለው በመሠረተው ክስ ነው፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ በበኩሉ በውሉ መሠረት ጉዳዩ በግልግል ዳኛነት ከሚታይ በስተቀር በዚህ ፍ/ቤት እንዲቀረብ



የተደረገው አላግባብ መሆኑን ገልጾ በመቃወም መልስ ከመሰጠቱ በተጨማሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 15803 ገላጋይ ለመምረጥ እንዲቻል ክስ ያቀረበ መሆኑን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ መልስ ሰጭ ብር 31.111.40/ሰለሣ አንድ ሺ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከአርባ ሣንቲም/ እንዲከፍልና ክርክሩ ላስከተለው ወጭና ኪሣራ በቁጥር 300/ሦስት መቶ ብር/ እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ በበላይ ፍ/ቤቶች ፀንቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሰበር እንዲታይለት ባቀረበው አቤቱታ ላይ ግራ ቀኞችን ባደረግነው ውል መሠረት አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት የሚታይ መሆኑ እየታወቀ የሥር ፍ/ቤት ይሄን አልፎ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረበው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሣ ነጥብ ያለው መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጐ የመ/ሰጭን መልስና የአመልካችን የመልስ መልስ አድምጧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በግራቀኝ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባቶች ሲነሱ በውላቸው መሠረት በግልግል ዳኝነት ይታያል የተባለው የውል ቃል ታልፎ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት እንዲታይ መደረጉ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ በዋንኛነት መመርመርና መወሰን ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡

ከጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታ እንደተረዳነው በአሁኑ አመልካች በመልስ ሰጭው መካከል ቀኑ በግልጽ ባልተመለከተ የውል ሰነድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለማድረግ ውል የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለሥራው ማስጀመሪያ የሚሆን ቅድመ ክፍያ የአሁኑ አመልካች ከመ/ሰጭ ላይ ከተቀበለ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባት በስምምነት መጨረስ ባለመቻላቸው የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭ በዞኑ ፍ/ቤት ክስ ከመመስረቱ በፊት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገላጋይ ዳኛ ለማስመረጥ ክስ የመሠረተ መሆኑን ታውቋል፡፡ በተጨማሪ የዞኑ ፍ/ቤት አሁን የቀረበውን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተቃውሞውን በብይን ውድቅ በማድረግ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት «በውሉ አንቀጽ 24 መሠረት ግራቀኙ እርስ በእርሣቸው ካልተስማሙ አንዱ ወገን በሕግ ወይም በሽምግልና መጠየቅ ይችላል፡፡» ይላል እንጂ ጉዳዩ በሽምግልና ብቻ ይታያል ተብሎ የተቀመጠ ግዴታ ስለሌለ ተቃውሞውን አልተቀበልነውም የሚል መሆኑን ፍ/ቤቱ በ9/1/95 ከሰጠው ብይን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የውሉን አንቀጽ 24 እንደመረመረው ተዋዋይ ወገኖች በመካከል አለመግባባቶች ከተነሱ ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣ ይህ ካልተቻለ ጉዳዩ በገላጋይ ዳኝነት የሚዳኝ ስለመሆኑ በሚገባ ተገንዝቧል፡፡

ይህ ሁኔታ በግልጽ ሰፍሮ እያለና በሌላ ፍ/ቤትም አስቀድሞ ክስ የቀረበለት መሆኑ ለዞኑ ፍ/ቤት የተገለፀለት ቢሆንም ፍ/ቤቱ ለመቀበል ሣይፈቅድ ቀርቷል፡፡ እንደሚታወቀው ተዋዋይ ወገኖች ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች በቀር የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የሕጉን አግባብ ተከትለው የተቋቀሙት ውሎች ደግሞ ባቋቋሟቸው ሰዎች ላይ መብትና ግዴታን ስለሚጥሉ እንደሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1731(1) ይደነግጋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአሁኑ አመልካችና መልስ ሰጭ መካከል የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ለመስራት በተደረገው ውል በአንቀጽ 24 ላይ አለመግባባቶች በግልግል ዳኞነት የሚታዩ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቶ እያለ ፍ/ቤቱ የውሉን አንቀጽ እርሱ በመሰለው ብቻ ተርጉሞ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡